# እንኳን ጌታ ለ2018 ማዜማ በሰላም አደረሳችሁ!
# አዲሱ አመት መልካም የበረከት አመት ይሁንላችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአዲስ አመት ፕሮግራም

የችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት በብረሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ማዕድ በመቁረስ፣ በጸሎት፣ በአምልኮ፣ ቃሉን በመካፈልና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የአዲስ አመት ማዜማ ፕሮግራምን በጋራ ያካሂዳሉ። ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን።

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለመስጠት ቃል የገባችሁ ደግም ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
| --- | --- |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

## መልካም አዲስ አመት ይሁንልን!




"በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ፥ ምድረ በዳውም ስብን ይጠግባል።"
(መዝ. 65፡11)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**December 31, 2017** | **ታኅሣሥ 22፣ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ............. | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥
ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። እነርሱ
ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ
ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጐናጸፊያም
ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል፤ **አንተ ግን**
**ያው አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።**

(መዝ. 102፡ 25-27)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኅ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

## የማይሻገረው እንዳይሻገር!

*“በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?*
*(2ቆሮ 13፡5)*

እንኳን ጌታ ለ2018 ዓመተ ምህረት ዋዜማ በሰላም አደረሳችሁ። ቀናት ቀናትን ወልደው አሮጌ አመት አልፎ በአዲስ አመት ሲተካ በቸርነቱ አመትን የሚያቀዳጀውን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። (መዝ. 65፡11) እያንዳንዱ አመት ከርሱ የምንቀበለው ጸጋና በረከት ነው። ዘመንን፣ እድሜን የሚሰጥ እርሱ ነው። ካሌብ ሕይወቱን ዞር ብሎ ተመልክቶ “እነዚህን አርባ አምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ” (ኢያሱ 14፡10) በማለት ለኖረበት ዘመንና ለተሰጠው እድሜ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። እኛም ለተሰጠን አዲስ አመት፤ ለተጨመረልን እድሜ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። አሁንም ስለምንገባበት አዲስ አመት እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

አዲስ አመት በመጣ ቁጥር ብዙ ሰዎች የአዲስ አመት ውሳኔ ያሳልፋሉ። እንዳንዶች ክብደት ለመቀነስ፣ ሌሎች አካላዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ፣ ሌሎች ደግሞ ከተለያዩ ልማዶችና ሱሶች ነጻ ለመሆን ለራሳቸው ቃል ይገባሉ። ይህ በተግባር ላይ ከዋለ መልካም ነገር ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው እንደዚህ አይነቱ ውሳኔ እጅግም አይዘልቅም። እኛስ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ወደ አዲሱ አመት ስንገባ ምን እያሰብን ይሆን? የበለጠ ቃሉን ለማንበብ? የበለጠ ለመጸለይ? የበለጠ ሕብረት ለማድረግ? የበለጠ በአግልሎት ለመትጋት? መልካም ነው። በምናስበው አቅጣጫ እንከናወን ዘንድ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛልን።

በአንጻሩ ደግም ወደ አዲሱ አመት ስንገባ እራሳችንን ቆም ብለን መመርመርና መፈተሽ መልካም ነው። መጽሐፍ “በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ” ይለናል። እስቲ ቆም ብለን ወደ 2018 አብረውን ማለፍ የለባቸውም የምንላቸውን ነገሮች እናስብ። ምንድን ነው ካሮጌው አመት ጋር መቅረት ያለበት? ቅያሜ ካለን ቅያሜን ይዘን ወደ አዲሱ አመት አንሻገር። ቅያሜን ካሮጌው አመት ጋር ጥለነው በአዲሱ አመት ለአንዲስ ግንኙንት እንነሳሳ። ቶሎ የሚከበን የኃጢያት ልምምድ ካለ ተከትሎን ወደ አዲሱ አመት እንዳይሻገር በጌታ ፊት ጸጋን ብንጠቅ መልካም ነው። ወደ አዲሱ አመት ስንዘልቅ ከድካሞቻችን ጋር እንፋታ። ዳተኝነትን ጥለን ትጋትን ለመታጠቅ እንወስን። ማስንቆአችንን ይሰቀልን እናውርድ። ሰይፋችንን የጣልን እናንሳ። “እኔ ካባቶቼ አልበልጥም ብለን” ከክትክታ ዝፍ ስር የተኛን እንነሳ። ልብ እንበል እግዚአብሔር በልባችን ስንወስን ጸጋና ሞገስን ይሰጠናል።